# Pneumococcal Conjugate ክትባት (PCV13)

## ማወቅ የሚገባዎት

Many Vaccine information Statements are available in Spanish and other languages. See www.immunize.org/vis

Hojas de información sobre vacunas están disponibles en español y en muchos otros idiomas. Visite www.immunize.org/vis

## 1 መከተብ ለምን አስፈለገ?

መከተብ ህጻናትንና አዋቂዎችን ከ **pneumococcal በሽታ** ይከላከላል።

Pneumococcal በሽታ ከሰው ወደ ሰው በቅርብ ንክኪ የሚተላለፍ በባክቴሪያ የሚመጣ በሽታ ነው። የጆሮ ኢንፌክሽን የሚፈጥር ሲሆን አደገኛ የሆኑ ኢንፌክሽኖችን እንደ፡

- ሳንባ (pneumonia)፣
- ደም (bacteremia)፣ እና
- አእምሮንና ህብለ ሰረሰርን የሚሸፍን (meningitis) ሊፈጥር ይችላል።

Pneumococcal pneumonia በአዋቂዎች ይበልጥ የተለመደ ነው። Pneumococcal meningitis መስማት መሳንንና የአእምሮ ጉዳት የሚያስከትል ሲሆን ከሚያገኛቸው 10 ልጆች ውስጥ 1 ልጅ ይገድላል።

ሁሉም ሰው በ Pneumococcal በሽታ ሊያዝ ይችላል፣ ነገር ግን ከ 2 ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት እና ከ 65 በላይ የሆኑ አዋቂዎች፣ አንዳንድ የጤና ችግር ያለባቸው፣ እና ሲጋራ የሚያጨሱ የበለጠ ስጋት ውስጥ ናቸው።

ክትባት ከመኖሩ በፊት፣ በዩናይትድ ስቴትስ የታየው፡

- ከ 700 በላይ የ meningitis ክስተቶች፣
- ከ 13,000 በላይ የደም ኢንፌክሽኖች፣
- ከ 5 ሚሊዮን በላይ የጆሮ ኢንፌክሽኖች፣ እና
- 200 ሰዎችን ለሞት ዳርገዋል

pneumococcal በሽታ ካለባቸው ከ 5 ዓመት በታች ያሉ ህጻናት ታይቷል። ክትባቱ ከመጣ በኋላ፣ ከባድ የሆነ የ pneumococcal በሽታ ከህጻናት ላይ በ 88% ቀንሷል።

በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ እስከ 18,000 የሚሆኑ ትላልቅ ሰዎች በየዓመቱ በ pneumococcal በሽታ ይሞታሉ።

Pneumococcal ኢንፌክሽኖችን በ ፔኒሲሊን ወይም በሌላ መድኀኒት ማከም እንደበፊቱ ውጤታማ አይደለም፣ ምክንያቱም የበሽታው አንዳንድ ክፍሎች ከመድኃኒቱ ጋር ስለተላመዱ ነው። ይህም በሽታውን በክትባት መከላከልን ጠቃሚ ያደርገዋል።

## 2 PCV13 ክትባት

Pneumococcal conjugate ክትባት (PCV13 ተብሎ የሚጠራው) 13 ዓይነት የ Pneumococcal ባክቴሪያዎች ይከላከላል።

PCV13 የሚሰጠው ለ 2፣4፣6፣ እናከ 12-15 ወር ለሞላቸው ህጻናት ነው። ከ65 ዓመት በላይ ለሆኑ ሁሉም አዋቂዎች እና አንዳንድ የጤና ችግር ላለባቸው ከ 2 እስከ 64 ዓመት ውስጥ ላሉ እና ህጻናትና አዋቂዎችም የሚመከር ነው። ሀኪምዎ የበለጠ መረጃ ሊሰጥዎ ይችላል።

## 3 አንዳንድ ሰዎች ይህንን ክትባት መውሰድ የለባቸውም

ከዚህ በፊት ከወሰደው ክትባት፣ በፊት ከነበረ PCV7 ከሚባል የ pneumococcal ክትባት የተነሳ ህይወትን አደጋ ላይ የሚጥል አለርጂ የተነሳበት ወይም diphtheria toxoid (ለምሳሌ, DTaP) የያዘ የትኛውንም ክትባት የተከተበ PCV13 መከተብ የለበትም።

ከ PCV13 ይዘቶች ውስጥ ከባድ አለርጂ ያለበት ማንኛውም ሰው ክትባቱን መውሰድ የለበትም። ክትባት ላይ ያለው ሰው ከባድ የአለርጂ ምልክቶች ካሉበት ለሀኪምዎ ይንገሩ።.

ለክትባት የተቀጠረው ሰው ጥሩ ስሜት እየተሰማው ካልሆነ፣ ህክምና እንክብካቤ ሰጪዎ በዚያን ቀን ይከተቡ ወይም በሌላ ቀን ይሁን የሚለውን ይወስናል።

## 4 የክትባት አለርጂ ስጋቶች

ክትባትን ጨምሮ በሁሉም መድሀኒቶች አለርጂ የመፈጠር እድል አለ። እነዚህ መለስተኛ ሲሆኑ በትንሽ ቀናት ውስጥ በራሳቸው የሚጠፉ ናቸው፣ ነገር ግን በጣም ከባድ ህመም ሊፈጥር ይችላል።

PCV13 ተክትለው የመጡ ችግሮች በእድሜና በክትባት መጠን ልዩነት አላቸው። ህጻናት አካባቢ ብዙ ጊዜ የሚፈጠሩ ችግሮች፡

- ከሚከተቡት ግማሾቹ ድንዛዜ፣ ጊዜያዊ የምግብ ፍላጎት መቀነስ፣ የክትባቱ ቦታ መቅላት ያጋጥማቸዋል።
- ከ 3 ውስጥ 1 ሰው የክትባቱ ቦታ እብጠት ይከሰትበታል።
- ከ 3 ውስጥ 1 ሰው አነስተኛ ትኩሳት እና ከ 20 ውስጥ 1 ሰው ከ 102.2°F የበለጠ ትኩሳት ይከሰትበታል።
- ከ 10 ሰው ውስጥ 8 ሰው መረበሽ ወይም ብዥታ ይከሰትበታል።

አዋቂዎች ህመም፣ መቅላት፣ ክትባቱ ቦታ እብጠት፣ አነስተኛ ትኩሳት፣ ራስ ህመም፣ ብርድ ብርድ ማለት እና የጡንቻ ህመም ሪፖርት አድርገዋል።

PCV13 ን ከ inactivated flu ክትባት ጋር አንድ ላይ የሚወስዱ ልጆች ከትኩሳት የተነሳ ለሲዠር ሊዳረጉ ይችላሉ። የበለጠ መረጃ ለማግኘት ሀኪምዎን ይጠይቁ።

U.S. Department of Health and Human Services
Centers for Disease Control and Prevention

**የትኛውንም ክትባት ከወሰዱ በኋላ የሚያጋጥሙ ችግሮች፡**

- ከህክምና በኋላ፣ ክትባትን ጨምሮ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ራሳቸውን ይስታሉ። ለ15 ደቂቃ መቀመጥ ወይም መተኛት ራስን መሳት እንዲሁም በመውደቅ የሚመጣውን ጉዳት ይከላከላል። የድንዛዜ ስሜት፣ የእይታ ለውጥ ወይም ጆሮ ውስጥ ማቃጨል ከተሰማዎት ለሀኪምዎ ይንገሩ።
- አንዳንድ ተለቅ ያሉ ህጻናት እና አዋቂዎች ትከሻ ላይ ከበድ ያለ ህመም ሲሰማቸው የተወጉበት እጃቸውን ማንቀሳቀስ ያስቸግራቸዋል። ይህ አልፎ አልፎ የሚከሰት ነው።
- የትኛውም መድኃኒት ከበድ ያለ የአለርጂክ አፀፋዊ ምላሽ ሊያስነሳ ይችላል። ከክትባት የሚመጡ አለርጂኮች በጣም አልፎ አልፎ የሚከሰቱ ሲሆኑ ከ አንድ ሚሊዮን ክትባቶች በ 1 እንደሚከሰት ይገመታል፤ የሚከሰተቱትም ክትባቱ ከተሰጠ በኋላ ከጥቂት ደቂቃዎች እስከ ጥቂት ሰዓታት ባለው ጊዜ ውስጥ ነው።

ልክ እንደ ሌላው መድኅኒት፣ ክትባት በጣም ከባድ ጉዳት ወይም ሞት የሚያስከስትበት በጣም ጠባብ እድል አለ።

የክትባቶች ደህንነት ሁልጊዜ በቅርብ ክትትል ውሰጥ ነው። ለበለጠ መረጃ ይህን ይጎብኙ፡ **www.cdc.gov/vaccinesafety**/

## 5 አደገኛ የሆነ የአለርጂ ምልክት ቢኖርስ?

**ማየት ያለብኝ ምንድነው?**

- ስጋት የሆንዎበትን ነገር እንደ ከባድ የአለርጂክ ምልክት፣ ከፍተኛ ትኩሳት ወይም ያልተለመዱ ባህርያትን ይመልከቱ።

  የከባድ አለርጂክ ምልክቶች የሚያካትቱት ሽፍታዎች፣ የፊትና የጉሮሮ እብጠት፣ የመተንፈስ ችግር፣ ፈጣን የሆነ የልብ ምት፣ መደንዘዝ እና ድካም ናቸው—አብዛኛውን ጊዜ ከክትባት በኋላ ከትንሽ ደቂቃ እስከ ትንሽ ሰዓታት ይፈጠራሉ።

**ምን ማድረግ አለብኝ?**

- ከባድ የሆነ የአለርጂክ ምልክት ወይም ሊቆይ የማይችል አስቸኳይ ከመሰልዎት 9-1-1 በመደወል አቅራቢያዎ ወዳለው ሆስፒታል ይሂዱ። ካለበለዚያ ሀኪምዎ ጋር ይደውሉ።

  ከዚያ በኋላ የአለርጂው ምልክት ለ "Vaccine Adverse Event Reporting System" (VAERS) ሪፖርት መደረግ አለበት። ሃኪምዎ ይህንን ፋይል ሪፖርት ማድረግ አለበት ወይም እርስዎ ራስዎ የ VAERS ድረ ገጽን በ **www.vaers.hhs.gov**በመጠቀም ወይም በ **1-800-822-7967** መደወል ይችላሉ።

VAERS የህክምና ምክር አይሰጥም።

## 6 The National Vaccine Injury Compensation Program

የ National Vaccine Injury Compensation Program (VICP) የፌደራል ፕሮግራም ሲሆን በክትባት ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ካሳ የሚሰጥ ነው።

በክትባት ጉዳት እንደደረሰባቸው የሚያስቡ ሰዎች ስለ ፕሮግራሙ ለማወቅ እና መጠየቅ ለመሙላት በ **1-800-338-2382** ይደውሉ ወይም የ VICP ድረ ገጽን በ **www.hrsa.gov/vaccinecompensation** ይብኙ። የካሳ ጥያቄ ለመጠየቅ የጊዜ ገደብ አለው።

## 7 እንዴት የበለጠ ማወቅ እችላለሁ?

- የጤና እንክብካቤ ሰጪዎን ይጠይቁ። እርሱ ወይም እርሷ የክትባቱን ማብራሪያ ወረቀት ወይም ሌላ የመረጃ ምንጭን መጠቆም ይችላል/ትችላለች።
- ለእርስዎ ግዛት የጤና ዲፓርትመንት ጋር ይደውሉ።
- Centers for Disease Control and Prevention (CDC) ን ያግኙ፡
  - **1-800-232-4636** (**1-800-CDC-INFO**) ይደውሉ ወይም
  - የ CDC ን ድረ ገጽ በ **www.cdc.gov/vaccines** ይጎብኙ

Vaccine Information Statement

# PCV13 Vaccine - Amharic

Office Use Only

11/05/2015

42 U.S.C. § 300aa-26

Translation provided by Minnesota Department of Health